የሰ/መ/ቁ. 28154

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ አለሙ ኢብሳ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ የምስራች ደሳለኝ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን በፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪና በፍርድ ባለእዳዎች እና አቶ ካሊድ የሱፍ /2 ሰዎች/ መካከል የነበረው የፍርድ አፈጻጸም ክርክር በሥር ፍ/ቤት ቀጥሎ በከፍተኛ 5 ቀበሌ 12 ክልል በ1ኛ የፍርድ ባለእዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቁጥር 1267 የሆነው መጋዘን ተሽጦ ሕዳር 3 ቀን 1969 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል በማለት በቅድሚያ መጋቢት 30 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚያም በ15/2/97 ዓ.ም የአፈጻጸም ትእዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ የተረዳን ሲሆን 2ኛው የአፈጻጸም ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ ትእዛዝ የተሰጠበት መጋዘን ላይ መብት ያለኝ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ መጋዘን ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርቦ አፈጻጸሙን በጊዜው ይዞት የነበረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያው ለፍርድ ባለመብት እንዲደርስ በማድረግ አከራክሮ መቃወሚያው በአግባቡ አልቀረበም የሚልበትን ምክንያት በዝርዝር አስፍሮ ተቀባይነት የለውም ብሎ አስቀድሞ በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ መሰረት ይሄው መጋዘን ተሽጦ በውሳኔው



ከፍርድ ባለእዳዎች የሚፈለገው ገንዘብ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ የሥር ፍ/ቤትን ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ የተመለከተው የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት አፈጻጸሙን በመቃወም ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ለፍርድ ባለመብት ብቻ እንዲደርስ ተደርጐ የፍርድ ባለእዳዎች በዚህ ላይ ክርክራቸውን ሳያቀርቡ ትእዛዝ መስጠቱን አግባብነት በተመለከተ ነው፡፡

በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ በዚህ ንብረት ላይ አፈጻጸም ሊቀጥል አይገባም በማለት 3ኛ ወገኖች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 418/1/ መሰረት መቃወሚያ ሲያቀርቡ ተከራካሪ ወገኖች ይህንኑ መብት የሚቃወሙ ከሆነ ፍ/ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ እንደሚሰጥ ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 ከፍ ብሎ ከተመለከተውና ከቁጥር 419 ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ የተባለው መጋዘን የ1ኛ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ነው እንደተባለ በትእዛዙ ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ንብረት ላይ ተቃዋሚው የአሁን አመልካች አፈጻጸሙን በመቃወም አቤቱታ ሲያቀርብ ከላይ ከተጠቀሰው የሥነ ሥርአት ሕጉ ድንጋጌ አኳያ አቤቱታው ለፍርድ ባለመብቱና ለባለእዳዎች ደርሶ የሁሉንም ወገኖች ክርክር በመስማት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 419 መሰረት ፍ/ቤቱ ውሳኔ መስጠት ሲገባው አቤቱታው ለፍርድ ባለመብት ብቻ እንዲደርስ በማድረግ ለዚህ